# Learning by Ear 2013

**መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ -ከባድ አማራጮችን መጋፈጥ**

## EPISODE EIGHTEEN: በጭንቀት ውስጥ

**AUTHOR: Chrispin Mwakideu**

**EDITOR: Madelaine Meier, Ludger Schadomsky**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of scenes:**

**SCENE ONE: አቶ ጃለታ AND HIS WIFE RETURN HOME FROM WALK**

- **አቶ ጃለታ (M, 45)**
- **ወ/ሮ ዘውዲቱ (F, 35)**

**SCENE TWO: ንጉሴ DRIVING አቶ ጃለታ ’S CAR IN THE CITY**

- **ንጉሴ (M, 16)**
- **PEDESTRIAN (F, 30)**
- **STRANGER (M, 40)**
- **GROUP OF STRANGERS (M/F, MIXED AGE)**

**SCENE THREE: ምህረት MEETS ትዕግስት IN A CAFÉ**

- **ምህረት (F, 15)**
- **ትዕግስት (F, 15)**
- **WAITER**

## SCENE FOUR: ዳንኤል AND በለጠ IN THE SCHOOL LIBRARY

- ዳንኤል **(M, 16)**
- በለጠ **(M, 15)**

## 1. INTRO - NARRATOR:

ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ተከታታዮች። ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" የተሰኘው ድራማ 18 ኛ ክፍል ነው። በኑሮዋቸው አስቸጋሪ ውሳኔዎችን እንዲወስዱ የተገደዱትን አፍሪቃዊ ወጣቶች ንጉሴ ፣ ዳንኤል እና ምህረትን ተዋውቀናል። እስኪ በጥቂቱ መለስ ብለን እንቃኝ። …

ምህረት የዳንኤልን ጥሪ ተቀብላ እንዴት ተሸሽጋ ወደ ወንዶች ማደሪያ ክፍል እንደገባች ሰምተናል። ሁለቱ ወጣቶችም መቀራረብ ሲጀምሩ የዳንኤል ጓደኛ በለጠ የት/ቤቱ ርዕሰ መምህርት ክፍሎችን በመቆጣጠር ላይ እንደሆኑ አይቶ ለሁለቱ ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል። ዳንኤል ምህረትን ይዞ እንዴት ቁጥቋጦ ውስጥ እንደተሸሸገ በኋላ ላይም ትንሽ ጭንቀቱ መለስ ሲልለት እንደገና ወደተቋረጠው የፍቅር ግንኙነት ለመመለስ ሲሞክር ፍላጎቱ ሊሳካ እንዳልቻለ ተመልክተናል።:

2. ዳንኤል **(EP 17, LINE 24):** (…) " የምልሽ ይገባሻል አይደል። እዚህ ማንም አያየንም። ቁጥቋጦው ሸፍኖናል።

3. ምህረት **:** "ዳንኤል …አልችልም። በጣም አዝናለሁ። ለዚህ ዝግጁ አይደለሁም። በጣም አደገኛ ነው። እባክህ እንቆይ።"

4. ዳንኤል **(LINE 28):** " ስለዚህ ለእኔ ምንም ስሜት የለሽም ማለት ነው። ሁሉም ነገር በውሸት የተሞላ ነበር። ጥሩ አሁን ተረድቻለሁ። እኔ ደግሞ የምትወጂኝ መስሎኝ ነበር። **(+ LINE 30)** "የምትወጂኝ ቢሆንማ ኖሮ ጥቂት ፍቅር ታሳይኝ ነበር።"

5. ምህረት **:** "ግን… ዳንኤል … እባክህ። ነግሬህ የለም እንዴ… "

ዳንኤል ምህረትን በጣም እያስጨነቃት ነው። በአቋማ ትፀና ይሆን ወይንስ እጁ ውስጥ ያስገባታል? በሌላ በኩል ንጉሴ ፤ ምህረት ለዳንኤል መወሰኗ አልተዋጠለትም። ስለሆነም እንዴት አድርጎ ልቧን እንደሚረታ እያቀደ ነው። **(KW BEGIN)**

6. ንጉሴ **(LINE 113):** "በጣም አሪፍ! እኔ ከዳንኤል እንደምሻል ለምህረት አሳያታለሁ። እንዴ በመኪና ከወሰድኳት ያንን ጭንቅላተ ቢስ ትረሳዋለች።

7. **SFX: CAR ENGINE STARTS**

8. ንጉሴ : "ያያያ መንገዱን ይዘህ ንካው።" **(KW END)**

ንጉሴ ምህረትን ለመማረክ የወላጆቹን መኪና ሰርቋል። ሙከራው ይሳካለት ይሆን? መድረኩ ተሰናድቷል። ዘና በሉና 18ኛውን ክፍል ተከታተሉ። ርይሱ « በጭንቀት ውስጥ» ይሰኛል። የንጉሴ ወላጆች ሰፈር ሰው ጠይቀው ገና ቤት መግባታቸው ነው።

**SCENE ONE: አቶ ጃለታ AND WIFE RETURN HOME FROM WALK**

9. **SUBURB ATMO IN THE EVENING**
10. **SFX: GATE BEING OPENED FROM THE OUTSIDE**
11. **SFX: FOOTSTEPS OF TWO PEOPLE APPROACHING**
12. አቶ ጃለታ : **(relaxed)** ወጣ ብለን መምጣታችን ጥሩ ነበር። በሰበቡም የሳምራዊትን እናት ጠይቀን መጣን። መቼም ከህመሟ በቅርቡ ታገግማለች።
13. ወ/ሮ ዘውዲቱ: **(also relaxed)** አዎ! ደሞ አምካኬን ምን ይሳነዋል። **(notices car missing)**
14. **SFX: FOOTSTEPS STOP**
15. ወ/ሮ ዘውዲቱ : ጃለታ አንተም የተለየ ነገር ልብ ብለሃል?
16. አቶ ጃለታ : **(shocked)** ይሄማ አይሆንም። መኪናዬ የለችም።

17. **ወ/ሮ ዘውዲቱ:** **(panicking)** ጃለታ ! ሌቦቹ ናቸው። እንደገና ዘርፈውን ሄዱ። እረ ለመሆኑ … ንጉሴ የታለ ?! ልጃችንን አንድ ነገር አድርገውት እንዳይሆን ደግሞ።

18. **አቶ ጃለታ :** **(trying to be brave)** የንጉሴ እናት ቆይ ረጋ በይ። ቀስ ብለን ወደ ውስጥ እንዝለቅ እና እንይ።

19. **ወ/ሮ ዘውዲቱ:** **(defensive)** በፍፁም! ወደ ውስጥ ልንገባ? አልሞከረውም። እንደገና የሌቦቹን ፊት ማየት አልፈልግም። የበፊቱ ይበቃኛል።

20. **አቶ ጃለታ :** ጥሩ አንቺ እዚሁ ቆይ። እኔ ስጮህ ከሰማሽ ወደ ውጭ ሂጂና ርዳታ ጥሪ።

21. **SFX: FOOTSTEPS SLOWLY APPROACHING**

22. **SFX: DOOR BEING UNLOCKED**

23. **አቶ ጃለታ:** **(calls out cautiously)** ንጉሴ !… ልጄ… አሁንም እክፍልህ ነው ያለኸው? ንጉሴ ? መጥተናል።

24. **SFX: FOOTSTEPS ON CARPET**

25. **SFX: DOOR AT OTHER SIDE OF THE ROOM OPENING**

26. **አቶ ጃለታ :** **(cursing)** የለም። እዚህ የለም።

27. **SFX: FOOTSTEPS WALKING AWAY IN A HURRY**

28. **አቶ ጃለታ**: **(to himself)** ይሄማ እውነት ሊሆን አይችልም። እነዚያ ሌቦች ተመልሰው መጥተው ነበር ማለት ነው? ግን እቃዎቹ በሙሉ ትተናቸው እንደሄድን ነው።…

29. **ወ/ሮ ዘውዲቱ:** **(thinking loud)** ጃለታ … ንጉሴ መኪናዋን ወስዶ ይሆን?

30. **አቶ ጃለታ :** አንቺ ደግሞ እንዴት ብሎ? መንጃ ፍቃድ እንኳን የለው።

31. **ወ/ሮ ዘውዲቱ :** **(nervous)** እንደውልለት። የሆነ መጥፎ ነገር እንደደረሰ ይሰማኛል።

32. **MUSIC INTERLUDE**

**SCENE TWO: ንጉሴ DRIVING አቶ ጃለታ ’S CAR IN THE CITY**

**33. SFX: CAR DRIVING FAST, RADIO PLAYING LOUD AGGRESSIVE MUSIC**

**34. SFX: OCCASIONAL HOOTING**

**35.** ንጉሴ : **(thinking aloud)** የእኔ ውድ ምህረት መቼም እዚህ መኪና ውስጥ ሆኜ ብታዪኝ የኔ ለመሆን አታንገራግርም ። ትዕግስት እውነቷን ከሆነ እና ምህረት ዳንኤልን የመረጠችው ለገንዘቡ ስትል ከሆነ፤ አንዴ በዚህ መኪና እስከማንሸራሸራት ድረስ ብቻ ነው። …

**36. SFX: MOBILE PHONE RINGING INSIDE CAR**

**37.** ንጉሴ : **(shocked)** ማን ሊሆን ይችላል? **(worried)** ወይኔ የእማዬ ቁጥር ነው። ከመቼው እቤት ደረሱ። ወይ ጉዴ። አሁን ያደረኩትን እንዴት ነው የምገልፅላቸው? … በቃ… ወደቤት መመለስ አለብኝ። **(sighs)**

**38. SFX: MUSIC TURNED OFF**

**KW BEGIN**

**39. SFX: BEEP AS CALL IS TAKEN**

**40.** ንጉሴ : **(answers phone while driving, guilty)** ሄሎ… እማ በጣም ይቅርታ። … አባዬን… ይቅርታ አድርግልኝ በይው… እሺ። መኪናዋን ይዤ እየመጣሁ ነው። … ለሙከራ … ነበር. … እሺ? መጣሁ ትንሽ ነው የቀረኝ ልደርስ።

**41. SFX: BEEP AS CALL IS ENDED**

**KW END**

42. **SFX: CAR MAKES QUICK U-TURN**

43. **SFX: LOUD EMERGENCY BRAKE**

44. **SFX: THUDDING SOUND**

45. ንጉሴ : **(totally terrified)** ወይኔ ጉዴ የምን ድምፅ ነው የሰማሁት።

46. **SFX: CROWD MURMURING AS THEY SLOWLY GATHER**

47. ንጉሴ : **(shocked)** ወይኔ ሰው… ገጭቻለሁ መሰለኝ። … ወይኔ!… ማንንም አላየሁም ነበር።

48. **STRANGER: (voice outside the car, shouting from the crowd)** እንዳችሁ ቶሎ በሉና አምቡላንስ ጥሩ። ለፖሊስም አሳውቁ። ሹፌሩ ደግሞ እንዳያመልጥ።

49. ንጉሴ : **(panting, breathing fast, in panic)** ምን አድርጌ ነው? ምን ሰርቼ ነው?

50. **SFX CAR DOOR OPENS**

51. **PEDESTRIAN: (on the street writhing in pain)** ኡኡኡ… ወይኔ እግሬ … እርዱኝ። **(continues whining throughout the scene)**

52. ንጉሴ : **(choking voice)** በጣም… አዝናለሁ… በእውነት… የእኔ ስህተት… አልነበረም።

53. **SFX:** ንጉሴ **GETS OUT OF THE CAR**

54. **SFX: CROWD REACTS IN SHOCK WHEN THEY SEE** ንጉሴ

55. **STRANGER:** አንተ ነህ መኪናውን ስትነዳ የነበረው?

56. ንጉሴ : **(stammers)** አዎን ግን … እኔ… አይደለሁም … ሞተች እንዴ?

**57. STRANGER:** አደገኛ ችግር ውስጥ ነው ያለኸው። ለመሆኑ ምን እንዳደረክ ታውቃለህ? ፖሊስ እስኪመጣ ጠብቅ። የመኪናውን ቁልፍ ስጠኝ።

**58.** ንጉሴ **:** **(pleading)** እባካችሁ አትምቱኝ። በጣም አዝናለሁ።

**59. MUSIC INTERLUDE**

## <u>SCENE THREE: ምህረት MEETS WITH ትዕግስት IN A CAFÉ</u>

**60. SFX: CAFE ATMO**

**61.** ትዕግስት **:** አስተናጋጅ። አስተናጋጅ!

**62. SFX: FOOTSTEPS - WAITER APPROACHES**

**63.** ትዕግስት **:** እባክህ እስኪለስላሳ አምጣልኝ።

**64. WAITER:** **(repeating)** ለአንቺስ?

**65.** ምህረት **:** አይ እኔ ምንም አልፈልግም። አመሰግናለሁ።

**66. SFX: FOOTSTEPS - WAITER LEAVING**

**KW BEGIN**

**67.** ትዕግስት **:** እ? ምህረት ለምን አንድ ነገር አታዝዢም?

**68.** ምህረት **:** አልጠማኝም ትዕግስት። ደግሞም ገና ለወሩ የሚበቃ ገንዘብ የለኝም።

**69.** ትዕግስት **:** ምን? እንዴት ሊሆን ቻለ?

**70.** ምህረት **:** ገንዘቤን ጨርሼ ነዋ።

**71.** ትዕግስት **:** ተጋብዘሻል። ስለገንዘቡ አታስቢ።

**72.** ምህረት **:** ትዕግስት አይሆንም አንቺ አትከፍይም።

**73.** ትዕግስት **:** ባክሽ ምንም አይደል። ደሞ ይሄ ትልቅ ነገር ሆኖ ነው ጓደኛዬ እኮ ነሽ ምህረት ?

**74.** ምህረት **:** አመሰግናለሁ።

75. **SFX: STEPS WAITER ARRIVES**

76. **WAITER:** ይኼው መጠጥሽ።

77. **SFX: BOTTLE PLACED ON TABLE**

78. ትዕግስት : ምን ትጠጫለሽ ምህረት ?

79. ምህረት : ሚኒራል ውሃ አምጣልኝ።

80. **WAITER:** እሺ።

81. **SFX: STEPS WAITER LEAVES**

**KW END**

82. ትዕግስት : እሺ እስቲ ከዳንኤል ጋ የነበረሽ ቀጠሮ እንዴት ነበር?

83. ምህረት: **(defensive)** ቀጠሮ አልነበረም... እንዲሁ... ነው የተገናኘነው።

84. ትዕግስት: **(sarcastic)** ነው እንዴ። እሺ! እንዴት ነበር ከዳንኤል ጋ ? ሁለታችሁም ... ያው ይገባሻል አንትን አላችሁ...

85. ምህረት : **(defensive)** ምንም አላደረግንም ትዕግስት ... ቅዠት ነው የሆነብኝ።

86. ትዕግስት : ቅዠት? ምን ስለተፈጠረ?

87. ምህረት : ወይጉድ... ብታይ የት/ቤት ኃላፊዋ ልትይዘን ነበር። ለትንሽ ነው ያመለጥነው።

88. ትዕግስት: **(alarmed)** ትቀልጃለሽ? አትይኝም። እንዴት ሆኖ?

89. ምህረት : **(whispers)** ዳንኤል ክፍል ነበርን። እጄን ስቦ አጠገቡ እንድቀመጥ ፈለገ።

90. ትዕግስት: **(excited)** አዩዩዩ ... የሆነ ዱርዬ ልጅ... ዱሪዬ ልጃገረድ...

91. ምህረት: ልቤ እንዴት ሲመታ እንደነበር ብታይ **(imitates sound)** ድው ድው ድው.... ምን ማድረግ እንዳለብኝ እንኳን አላውቅም ነበር።

92. **SFX: STEPS WAITER ARRIVES**

93. **WAITER:** ይሄው ውሃሽ።

**94. SFX: BOTTLE PUT ON TABLE**

**95. SFX: STEPS WAITER LEAVES**

**96.** ትዕግስት: አመሰግናለሁ። (to ምህረት ) እሺ. ቀጥይ ምህረት ። እንዴት ልብ አንጠልጣይ ነው። እና ርዕሰ መምህርቷ በሩን በርግደው ገቡ?

**97.** ምህረት : አቤት የአንቺ አስተሳሰብ ደግሞ ትዕግስት። በለጠ በሩን አንኳክቶ ኃላፊዋ እየመጡ እንደሆነ ነገረን። አንዳንድ ጊዜ መኝታ ቤታቸውን ለመቆጣጠር ይመጣሉ። በለጠ እና ዳንኤል ቀይ ካርድ ነው የሚሉት። ከዛ ዳንኤል እንደምንም ሾልከን እንድንወጣ አደረገ እና አመለጥን። በቃ ይሄው ነው።

**98.** ትዕግስት: **(unsatisfied)** በቃ? ሌላ ምንም ነገር አልተፈፀመም?

**99.** ምህረት: **(shyly)** ምንም አልሆነም። እድለኛ ነኝ አይደል?

**100.** ትዕግስት : ባክሽ አትፎግሪ... እና አልተሻሻችችሁም ወይንም አልተሳሳማችሁም?

**101.** ምህረት: **(defensive)** አይ! ዳንኤል ... ግን... ፈልጎ ነበር... እንዴት ብዬ ልንገርሽ?... ራሴን እንድሰጠው ፈልጎ ነበር። ግን እምቢ አልኩት።

**102.** ትዕግስት: **(shocked)** እምቢ አልሽው? እንደማትፈልጊ ነገር?

**103.** ምህረት : አዎ! እና አሁን በጣም ነው የተናደደብኝ። በቃ ተው ይቅርብን እንቆይ ስላልኩት ብቻ።

**104.** ትዕግስት : እንቆይ? ወይ ምህረት ! አንድ ነገር ልንገርሽ። አሁን እኮ አንቺ ትልቅ ልጅ ነሽ። የወር አበባ ማየት ጀምረሻል። የሚቀጥለው የዕድገት ደረጃ ክብረ ንፅህናሽን ማጣት ነው። ብትቆይ እድገትሽን ታዘገያለሽ። ይህንን ታውቂያለሽ አይደል?

**105.** ምህረት: **(confused)** ዕርግጠኛ ነሽ ትዕግስት?ይሄንን ሁሉ የት ነው የተማርሽው? እኔ የማውቀው እስካገባ ድረስ መጠበቅ እንዳለብኝ ነው።

**106.** ትዕግስት: **(sarcastic laugh)** ምህረት ልክ በጥንት ጊዜ ያለ ሰው ሆንሽብኝ። ያንቺ ድንግልና በመጨረሻ የት ያደርስሽ መሰለሽ? ኧ ምን አልባት ዘውድ ልትጭኚ? የራስሽ ጉዳይ። እንደ ጓደኛ ግን ላስጠነቅቅሽ ብዬ ነው።

**107. SFX: DRINKS FINISHED AND STRAWS MAKING SOUNDS**

**108.** ትዕግስት : **(shouts)** ይቅርታ እባክህ ሂሳብ አምጣልኝ።

**109. MUSIC INTERLUDE**

**<u>SCENE THREE: ዳንኤል AND በለጠ IN THE SCHOOL LIBRARY</u>**

**110. SFX: LIBRARY ATMO**

**111. SFX: PAGE OF A BOOK BEING TURNED**

**112.** በለጠ: **(in hushed tone)** ዳንኤል እሺ የዛን ቀን ከምህረት ጋ እንዴት አለፈ? ከዚያን ቀን ወዲህ እንደድሮው አይደለህም።

**113.** ዳንኤል : ስለሱ ባናወራ ይሻላል በለጠ ። ቅር አይልህም አይደል።

**114.** በለጠ: **(still pressuring)** ግን እንዴት ነው… ስትል እንደነበረው … ማሩን ለመቅመስ ቻልክ?

**KW BEGIN**

**115.** ዳንኤል : በለጠ ቤተ መፅሀፍት ውስጥእኮ ነው ያለነው። ስለዚህ ሌላ ጊዜ ልናወራ አንችልም?

**116.** በለጠ : **(prodding further)** ተይ ተይ ተይ… በርግጥም ተሳክቶልሻል… አንተ ዕድለኛ የላቦሪያ ተወላጅ። በል ንገረኝ ። እንዴት ነበር?

**117.** ዳንኤል: **(irritated)** በለጠ !እስኪ በእናትህ አረፍ። አትረብሸኝ። ለማጥናት እየሞከርኩ ነው።

**118. SFX: PAGE OF A BOOK TURNED**

**119.** በለጠ : እእ… ጥሩ ሁኔታ ላይ ያለህ አትመስልም። ስለእዚህ ምናልባት ልክ አይደለሁም መሰለኝ። እና ከምህረት ጋ የዛን ቀን ጎል አላስገባችሁማ? አይይይ… ግን ቢያንስ መሳሳም ምናምን አስቆጥራችኋል አይደል።

**KW END**

**120.** ዳንኤል : ምንም ነገር አልነበረም በቃ። ምንም አይነት መሳሳም፣ መተቃቀፍ ወይንም ሌላ ነገር። ምህረት በቅታኛለች ! አሁን ደስ አለህ?አሁን እዚህ ስለመጣንበት ጉዳይ ትኩረት ልንሰጥ እንችላለን? አመሰግናለሁ።

**121.** በለጠ : ኦ… ይቅርታ ዳን!

**122. MUSIC INTERLUDE**

**123. <u>OUTRO - NARRATOR:</u>**

ዳንኤል ከምህረት ጋ ሳይሳካለት ስለቀረው ጉዳይ ማውራት አልፈለገም። በሽቋል። እና ታሪኩ እንዴት ይቀጥል ይሆን? ምህረት እና ዳንኤል ስላጋጠማቸው ችግር መፍትሄ ለማግኘት ዳግም ይወያዩ ይሆን? በሌላ በኩል በመንገድ ላይ የነበረ ሰው የገጨው ንጉሴስ ምን ይሆን? በቅርቡ እንደርስበታለን። ይህን 18ኛ ክፍል ድራማ ደግመው መስማት ከፈለጉ dw.de/lbe የተሰኘዉን ድረ- ገፃችን ይጎብኙ፤ አልያም በፌስቡክ አድራሻችን ላይ ይከታተሉ። እስከሚቀጥለዉ ጊዜ፤ ጤና ይስጥልን።